# “በደቡብ ወሎ ዞን የአካባቢ መራቆት በአርሶ አደሩ የኑሮ መተዳደሪያ በስደተኝነት ላይ ያመጣው ውጤት”

## ሚግሶኮ/ የጥናት ቡድኑ እና የአጋር አካላት ዎርክሾፕ በደቡብ ወሎ፤ መጋቢት 2011 ዓ.ም


ጁሊያን ግሩዝ[1] ፤ ዶ/ር ጁሌ ቶበር[1] ፤ ዶ/ር ካትሊን ኽርማንስ[1] ፤ እንደሻው ካሣ[2]

[1] ሄልምሆልትዝ የአካባቢ ምርምር ማዕከል የኢኮሎጂና የምድር ስነ ውበት ኮምፒዩቴሽናል ክፍል፤ ሌፕዚግ፣ ጀርመን

[2] የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ኮሚሽን (ኢወቤመ ልማአኮ)


## በምርምሩ ላይ ስለ ተሳተፉ አባላት ማንነት

እኛ ሄልምሆልትዝ የአካባቢ ምርምር ማዕከል የኢኮሎጂና የምድር ስነ ውበት ኮምፒዩቴሽናል ክፍል፤ ሌፕዚግ፣ ጀርመን ውስጥ የምንሰራ የተመራማሪዎች ቡድን ነን። በምርምራችንም የአካባቢ መራቆት እና የሰዎች ስደት መነሻ ምክንያቶችንና ትስስሮችን በጥናቶቻችን ለመረዳት ጥረት አድርገናል። ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እንደመምጣታችን በጉዳዩ ላይ የተሻለ መረዳት እንዲኖረን በጥናታችን የተለያዩ ስልቶችን ለማቀናጀት ሞክረናል። ባለፉት የቅርብ አስርተ አመታት በመላው አለም በሚሊዮኖች የሚገመቱ ህዝቦች በአካባቢ መራቆት ምክንያት ተሰደዋል።

ይህም ሁኔታ ከህዝብ ቁጥር መጨመርና ከአካባቢ መራቆት መባባስ ጋር ተያይዞ የስደተኛውም ቁጥር እንደሚጨምር ይጠበቃል።

ለምንና በምን ሁኔታዎች ነው ሰዎች የሚሰደዱት? የአካባቢ መራቆትስ ለዚህ ምን አይነት ሚና ነበራቸው? በኢትዮጵያ ያለውን የአካባቢመራቆትና ለሰዎች መሰደድ መነሻ




ከግራ ወደ ቀኝ ዶ/ር ጁሌ ቶበር፤ ዶ/ር ካትሊን ኽርማንስ፤ ጁሊያን ግሩዝ፤ ቻርሎቴ ዌይደርከኽር

የሆነውን ምክንያት ለማወቅ ስደተኝነትን በተለያየ መንገድ ለመረዳት ሞክረናል።


በደቡብ ወሎ የገጠር ቀበሌዎች ባደረግነው የመስክ ጥናት፤ ከነዋሪዎችና ሌሎች አካላት ጋር የቡድን ውይይትና የግለሰቦች ቃለ መጠይቆችን በማድረግ የአካባቢ መራቆትና ስደት ያለውን ትስስር ውጤት በዚህ ዎርክሾፕ በማቅረብና ከተሳታፊዎች ጋርም ውይይት በማድረግ ሃሳቡን ማዳበር ፈልገናል። ጥናታችንምከኢትዮጵያወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ኮሚሽን ጋር በመተባበር የተሰራ ነው።

## አላማ

የጥናታችን አላማ፡ የደቡብ ወሎ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው ከመሬት መራቆትና ለምርት ምቹ ካልሆነ የዝናብ ስርጭት ጋር ተያይዞ ለመሰደድ እንዲወስኑ የሚያደርጋቸውን ሁኔታ መረዳት ነው።

በመሆኑም የተለያዩ የአየር ንብረት ተፅዕኖዎች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሰዎችን የስደት ባህሪያት በጥናት ውስጥ በማካተት ትኩረት ተሰቷቸው ተዳሰዋል፡

ጥናቱ የተሰራበት አካባቢ





**ደሴ ዙሪያ ወረዳ**
- አደይ

**ኩታበር ወረዳ**
- አላንሻ
- አምባ ጊቢ
- ቁንዲ

**ለጋምቦ ወረዳ**
- ጪንጫ

**ቃሉ ወረዳ**
- ተቃቄ

## የጥናት ስልት





ጥናታችን የሚያደርገው አስተዋፅኦ፡
የተለያዩ መረጃዎችን ከብዙ ቃለመጠይቆች ማለትም ስደት ከሄደባቸውና ካልሄደባቸው ቤተሰቦች፣ ከአካባቢው መሪዎች ጋር እና ከሌሎች ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ጋር በመነጋገር የተገኙትን መረጃዎች ስልታዊ በሆነ መንገድ መተንተን አስችሏል። ጥናቱ በስድስት ቀበሌዎች ከቆላ እስከ ደጋ ባሉ የአየር ንብረት ከባቢዎች ላይ ተካሄዷል።


እነዚህ አካባቢዎችም በመሬት መራቆት ደረጃቸው፣ በሚያገኙት የዝናብ ወቅት፣የመንገድ አውታራቸው እና ለገበያ ባላቸው ቅርበት መነሻነት የተመረጡትን ቀበሌዎች የተለያዩ ያደርጋቸዋል። ከፍታቸውም ከ400 እስከ 3700 ሜትር ከባህር ወለል በላይ በመሆኑ ቦታዎቹ በደጋ፣ወይና ደጋና ቆላ አየር ንብረት ክልሎችን ያካተተ ነው።

## በደቡብ ወሎ የአካባቢ መራቆትና በገጠር የኑሮ መተዳደሪያ ላይ ያለው ወጤት

የዝናብ ስርጭት (ደሴ)




የበልግ እና ክረምት ዝናብ መጀመሪያ ወቅት መቀየር (ደሴ)




- የለም አፈር መሸርሸርና በቦሮቦር የሚጠቃው መሬት መጨመር
- የበልግ ወይም የክረምት ወቅት መዘግየት ወይም መቅረት
- የእርሻ መሬት ከምርት ስራ ውጪ መሆን
- ውርጭ እና ተባይ
- በፖሊሲ ዙሪያ ያሉ ተግባራት

**የምርት መቀነስ ወይም መጥፋት**

**የእንስሳት ቁጥር መቀነስ ወይም የእንስሳት ሞት**

## የአካባቢ ለውጥንና መራቆትን የምንቋቋምበት ስልት

**ስደት**

- እንስሳትን መሸጥ
- መጠበቅና ፈጣሪን መለመን
- የሰብል አመራረት ስልት
- የገቢ ማግኛ ምንጮችን ማስፋት
- የአፈርና ውሃ ጥበቃ ተግባራት
- በዝናብ መጥፋት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት በሌላ የዝናብ ወቅት ማካካስ
- ከመንግስት ወይም ከሌሎች አካላት የሚገኝ ድጋፍ

- ስደት በተለያየ የእድሜ ክልል ባሉ ሰዎች፣ ፆታን ሳይለይ እና በተለያየ የኑሮ ደረጃ ላይ ባሉት የህበረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ላይ ይከሰታል
- ስደት በገጠር፣ በከተማ፣ በጊዜያዊነት፣ በቋሚነት እንዲሁም በሃገር ውስጥ እና ወደ ውጭ አገር ሊሆን ይችላል።

**ደቡብ ወሎ** → አፋር ክልል, ጂቡቲ, አረብ አገራት, ደሴ, ኮምቦልቻ, አዲስ አበባ, ጂማ

→ ስደት ከአካባቢ ለውጥና መራቆት ጋር በተያያዘ የሚፈጠረውን የኑሮ መተዳደሪያ ችግር መቋቋሚያ ስልት ሊሆን ይችላል

## የደቡብ ወሎ የስደት ሁኔታ

**የደቡብ ወሎ ገጠራማው ክፍል**
- ከፍተኛ የመሬት መራቆትና የዝናብ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ መዛባት
- የእርሻ መሬት እጥረት
- ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር መጨመር
- የስራ እድል መታጣት

→ ሰዎች አካባቢያቸውን መልቀቅ መፈለግ

↓ ሁሉም ሰዎችግንመሰደድ አይፈልጉም! **ለምን? እነማን ናቸው መልቀቅ የቻሉት?**

**በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሰዎች እንዲሰደዱ የሚያግዙ ጉዳዮች**
- ስደት ላይ ልምድ ያላቸው የቤተሰብ አባላት፣ጎረቤቶች እና ጓደኞች
- የገቢ ማስገኛ ዘዴዎቹ ከሰብልና ከእንስሳት ስራዎች ውጪ ሲሆኑ
- የክረምት ወቅት የሰብል ማምረቻ ወቅት መሆኑ

“በዚህ አካባቢ ብቸኛው የኑሮ መተዳደሪያ ግብርና ነው። ምንም ለውጥ አይታይም እኔ ደግሞ ህይወቴን ማሻሻል እፈልጋለው። ህይወት እዚህ ከባድ ነው። እናም እዚህ መሆንን አልፈልግም። ”

“ከብዙ መሬት ብዙ ምርት ይገኛል። እናም ልጆቼ እዚሁ መቆየት ይችላሉ ”

→ የማህበረሰብ ትስስሮች እንዲሁም የኑሮ መተዳደሪያ ዘዴዎች ስብጥር ለሰዎች መሰደድ ወሳኝ ሚና አላቸው


**አድራሻ፡**
የዲዛይን ቅንብር፡ ሃና ፍሬድሪክ

ካትሊን ኽርማንስ
@ kathleen.hermans@ufz.de

ጁሊያን ግሩዝ
@ juliane.groth@ufz.de

የፕሮጀክቱ ዌብ ሳይት
https://www.ufz.de/migsoko/



MIGSOKO · HELMHOLTZ CENTRE FOR ENVIRONMENTAL RESEARCH – UFZ · FONA Social-Ecological Research BMBF · pecs